# የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

## ፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ
## FEDERAL NEGARIT GAZETTE
## OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

ሃያ አምስተኛ ዓመት ቁጥር ፶፬
አዲስ አበባ ሚያዚያ ፱ ቀን ፪ሺ፲፩ ዓ.ም

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

25th Year, No. 54
ADDIS ABABA ,17th April, 2019


**ማውጫ**


አዋጅ ቁጥር ፩ሺ፩፻፳፭/፪ሺ፲፩ ዓ.ም

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መንግስት እና በህንድ ሪፐብሊክ ሪፐብሊክ መንግስት መካከል በኮሙኒኬሽን፣ኢንፎርሜሽን እና ሚዲያ ዘርፍ የተፈረመው የትብብር ስምምነት ማፅደቂያ አዋጅ ………………….…………………………………ገጽ ፲፩ሺ፪፻፲፬


**Content**


Proclamation No 1125/2018

Agreement between the Goverrnment of the Federal Democratic Republic of Ethiopia and the Government of the Republic of India in the field of Communication ,Information and Media Ratification Proclamation…………………………………...Page 11214


### አዋጅ ቁጥር ፩ሺ፩፻፳፭/፪ሺ፲፩

### በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መንግስት እና በህንድ ሪፐብሊክ መንግስት መካከል በኮሙኒኬሽን ፣ኢንፎርሜሽን እና ሚዲያ ዘርፍ የተፈረመውን የትብብር ስምምነት ለማፅደቅ የወጣ አዋጅ

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መንግስት እና በህንድ ሪፐብሊክ መንግስት መካከል በኮሙኒኬሽን፣ኢንፎርሜሽን እና ሚዲያ ዘርፍ የትብብር ስምምነት መስከረም ፳፭ ቀን ፪ሺ፲ ዓ.ም በአዲስ አበባ የተፈረመ በመሆኑ፤

ይህንኑ ስምምነት የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት መጋቢት ፳፬ ቀን ፪ሺ፲፩ ዓ.ም ባደረገው ስብሰባ ያፀደቀው በመሆኑ፣

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግስት አንቀጽ ፶፭ (፩) እና (፲፪) መሠረት የሚከተለው ታውጇል፡-

### PROCLAMATION NO. 1125/2019

### A PROCLAMATION TO RATIFY THE AGREEMENT BETWEEN THE GOVERNMNET OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA AND THE GOVERNMENT OF THE REPUBLIC OF INDIA ON COOPERATION IN THE FIELD OF COMMUNICATION ,INFORMATION AND MEDIA

**WHERE AS,** th*e* Government of the Federal Democratic Republic of Ethiopia and the Government of the Republic of India have signed an agreement on Cooperation in the field of Communication,Information and Media was signed in Addis Ababa, on the 5th day of October ,2017;

**WHERE AS**, the House of the Peoples' Representatives of the Federal Democratic Republic of Ethiopia has ratified the said agreement at its session held on the 2nd day of April, 2019 ;

**NOW THEREFORE,** in accordance with Article 55 (1) and (12) of the Constitution of the Federal Democratic Republic of Ethiopia, it is hereby proclaimed as follows:

**፩. <u>አጭር ርዕስ</u>**

ይህ አዋጅ "በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መንግስት እና በህንድ ሪፐብሊክ ሪፐብሊክ መንግስት መካከል በኮሙኒኬሽን፣ ኢንፎርሜሽን እና ሚዲያ ዘርፍ የተፈረመው የትብብር ስምምነት ማፅደቂያ አዋጅ ቁጥር ፩ሺ፩፻፳፭/፪ሺ፲፩ "ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።

**፪. <u>የስምምነቱ መፅደቅ</u>**

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መንግስት እና በህንድ ሪፐብሊክ መንግስት መካከል መስከረም ፳፭ ቀን ፪ሺ፲ ዓ.ም በአዲስ አበባ በኮሙኒኬሽን፣ኢንፎርሜሽን እና ሚዲያ ዘርፍ የተፈረመው የትብብር ስምምነት በዚህ አዋጅ ፀድቋል።

**፫.<u>አስፈፃሚ አካል</u>**

የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የጠቅላይ ሚኒስቴር ፅህፈት ቤት ይህን ስምምነት የማስፈፀም ሀላፊነት ተሰጥቶታል።

**፬.<u>አዋጁ የሚፀናበት ጊዜ</u>**

ይህ አዋጅ በፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡

**አዲስ አበባ መጋቢት ፱ ቀን ፪ሺ፲፩ ዓ.ም**

**ሳህለወርቅ ዘውዴ**

**የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ**

**ፕሬዝዳንት**

**1. <u>Short Title</u>**

This proclamation may be cited as "Agreement between the Government of the Federal Democratic Republic of Ethiopia and the Government of the Republic of India in the field of Communication, Information and Media Ratification Proclamation No.1125/2019."

**2. <u>Ratification of the Agreement</u>**

The Agreement between the Government of the Federal Democratic Republic of Ethiopia and the Government of the Republic of India on Cooperation in the field of Communication, Information and Media which was signed in Addis Ababa, on 5th day of October 2017 is here by ratified.

**3. <u>Implementing Organ</u>**

The Office of the Prime Minister of the Federal Democratic Republic of Ethiopia is hereby empowered to implement this agreement.

**4. <u>Effective Date</u>**

This Proclamation shall enter into force on the date of publication in the Federal Negarit Gazette.

**Done at Addis Ababa, this 17th day of April 2019.**

**SAHLEWORK ZEWDE**

**PRESIDENT OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA**